

# ፍትሕ ለአሰፋ አብርሃ

*ሕዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም*

**ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ**
**የኢፌዲሪ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር**
**አዲስ አበባ**

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፤

በሰሜን አሜሪካ የምንኖር የትግራይ ተወላጆች የአገራችንን የፍትህ ሥርዓት አፈፃፀም በማስመልከት በተለይም የኢፌዲሪን ሕገመንግሥት ከማክበርና ከማስከበር ብሎም የአገሪቱን ሕግ ከማስፈፀም አኳያ በአቶ ስዬ አብርሃና በቤተሰቦቻቸው ላይ በበቂ ማስረጃ ባልተደገፈና ባልተረጋገጠ ክስ፣ ሕጉ በሚያዘው መሰረት ዳኞች እንኳን ተሟልተው ባልተሰየሙበት የፍርድ ሂደት፣ የሕግ ከለላ መብትን በመንፈግ፣ የዜጎችን የዋስትና መብት ለመከልከል በወጣ አዲስ ሕግ ሕገመንግስታዊ መብትን በማገድ፣ የተወሰኑ የመከላከያ ምስክሮች እንዳይሰሙ በመከልከል፣ በተለየ ሁኔታ ለይቶ በማሰር፣ ጥፋተኝነታቸው ያልተረጋገጠ ዜጎችን ለዓመታት በእስራት በመቅጣት፣ በዳኝነት አለመሟላት እየተመካኘ የተፈፀመውን የተራዘመና የተጓተተ ኢፍትሃዊ አያያዝና አካሄድ እንደመነሻ ነጥብ በመያዝ፤ በአካልና በቴሌኮንፍረንስ ሰፋፊ ውይይቶችን በማካሄድ፤ ለኢፌዲሪ መንግሥት አስፈፃሚ ኣካላት፣ ለአገራችን የፌዴሬሽንና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች፣ እንዲሁም ለኢፌዲሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የሕግ አስፈፃሚ አካላት በደብዳቤና በአካል የአቤቱታና የተቃውሞ ድምፃችንን ስናሰማ መቆየታችን የሚታወስ ነው።

በአቶ ስዬ አብርሃ ከእስር መለቀቅ በአሜሪካ የምንኖር ፍትህ ወዳድ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማን ስንገልፅ፤ ፍትህ የሰፈነበትና የሕግ የበላይነት የተረጋገጠበት ሥርዓት

ለሕዝቦች መብት መከበርና ለአገር ሰላም ልማትና ዕድገት ዋስትና እንደመሆኑ፣ የአገራችን የሕግ አስፈፃሚ አካላት ብሎም የኢፌዲሪ መንግሥት ከሕዝብ የተነሳውን የፍትህ መነፈግ ብሶት በማዳመጥ፣ ከተንተተና ከተንዛዛ የፍትህ አፈፃፀም በኋላ በመጨረሻው ሰዓት ላይ በተገቢው ዳኛ በመሰየምና በአጫጭር ቀጠሮዎች በማስቻል፣ የአቶ ስዬ ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት እንዲያገኝ በመደረጉ፣ በተለይም ለአገራችን የሕግ አስፈፃሚ አካላት በአጠቃላይም ለኢፌዲሪ መንግሥት ስለፍትህ ያለንን አክብሮትና ምስጋናችንን እንገልፃለን፡፡

ሆኖም ግን፣ በአቶ ስዬ አብርሃ ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ምንም እንኳን በፍርድ ቤት የተላለፈ ውሳኔ በመሆኑ ብቻ ብናከብረውም፣ በበቂ ማስረጃ ያልተደገፈና በስማ-በለው 'ለወንድማቸው ሕገ-ወጥ ጥቅም ለማስገኘት አስነግረዋል' በሚል ከአሉባልታ ባልዘለለ ተራ ውንጀላ ብቻ የፖለቲካና ወታደራዊ ተክለ-ሰውነታቸውን ክብራቸውንና ንፅህናቸውን ለማጉደፍ በማለም፣ ብሎም ከስድስት ዓመት በላይ አለአግባብ የታሰሩበትን ጊዜ ለማካካስ የተሰራ በሚመስል የስሌት የቅጣት ውሳኔ መሰጠቱ በጣሙኑ አሳዝኖናል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ፣ የአቶ ስዬ አብርሃ ወንድም በመሆናቸው ብቻ በደርግ መንግሥት ለአስር ዓመታት የአለም በቃኝ እስራት ግርፋትና ግፍ የተፈፀመባቸው አቶ አሰፋ አብርሃ ዛሬም በአገራችን ፍትህ ሰፍኖ የሕግ የበላይነት ተረጋግጧል በሚባልበት ወቅት፣ ከአገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር በአንድነት በቦርድ አባልነት በሰሩበትና በአንድነት በወሰኑበት አሰራር አንድን ግለሰብ ነጥሎ በሌለ ጥፋት በወንጀለኛነት በመፈረጅ ለዓመታት እስራት መዳረግ፣ በግልፅ የሕግ የበላይነትን የጣሰና የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ሕገመንግስት የሚፃረር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አቶ አሰፋ አብርሃ ከመንግሥት በተሰጣቸው ኃላፊነት መሠረት ከአቶ ሶፊያን አህመድ የፕላንና የገንዘብ ሚኒስትር፣ ከአቶ መስፍን ለማ የጠቅላይ ሚንስትር የሕግ አማካሪ፣ ከዶ/ር ከበደ ታደሰ በሚኒስትር መዓርግ በወቅቱ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የማሕበራዊ ዘርፍ ኃላፊ፣ አቶ ማኅተመ ሰለሞን በወቅቱ የፍትህ ሚኒስትር፣ እና ከሌሎች የአገሪቱ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ጋር በቦርድ አባልነት ኃላፊነታቸውን ከመወጣት ባሻገር በግል በሰሩት የሥራ ኃላፊነት አይደለም የተወነጀሉትና ለእስራትና ለእንግልት የተዳረጉት፡፡ ይህንንም የቦርዱን የሕብረት አሰራርና ውሳኔ በማስመልከት እነዚሁ የቦርድ አባላት የነበሩት የአገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት በተከበረው ፍርድ ቤት ፊት ቀርበው በሕብረት ተስማምተው ይወስኑና ያስፈፅሙ እንደነበር ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፣

እንኳንስ በማስረጃ የተደገፈ ሕገወጥ አሰራር በሌለበት፣ የተከሰተ የአሰራር ጉድለትና ምዝበራ ቢኖርስ፣ በምን ዓይነት የሕግ ወይንም የአስተዳደር መስፈርትና መመዘኛ ነው በጋራ በተላለፈ ውሳኔ አንድ የቦርድ አባል በግል ስለሕብረት ውሳኔው በወንጀለኛነት ተጠያቂ የሚሆነውና ለእስርና ለእንግልት የሚዳረገው?

ይህም ብቻም አይደለም፤ አግባብነት በሌለው ሕገወጥ ውንጀላ በማስረጃ ባልተደገፈ ክስ የዘጠኝ ዓመት እስራት የተበየነባቸው አቶ አሰፋ አብርሃ የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ቁጥር 202 በሚያዘው መሠረት፤ ማንኛውም የሕግ ታሳሪ በቁጥጥር ስር ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በወህኒ ቤት የፈፀመው አንጻችም ጥፋት እስከሌለ ድረስ ከእያንዳንዱ ዓመት አራት ወር እየተሰላ በአመኩሮ ነፃ የመውጣት መብት እንዳለው ይደነግጋል። እውን መድህን ዋስትናችን ሕገመንግስታችንና የሕግ የበላይነት ከሆነ፤ መንግሥታችን ስለሚሊኒዬሙ መባቻ 'አደገኛና ፀረሕዝብ ወንጀለኛ' በማለት በፍርድ ቤት አስችሎ ለተፈረደባቸው ታሳሪዎች ሳይቀር የሕግ ድጋፍ እንኳን በሌለበት ምሕረት አደረግኩኝ በሚልበት ወቅት፤ በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ በግልፅ በተቀመጠው የዜጎች መብት መሰረት በአመኩሮ የስድስት ዓመት እስራታቸውን ከበርካታ ወራት በፊት ያጠናቀቁት አቶ አሰፋ አብርሃ አሁንም በእስር እንዲማቅቁ መደረጉ መንግስታዊ የሕገመንግስትና የሕግ ጥሰት ሆኖ አግኝተነዋል። ይህም አፈፃፀም የመንግሥት አስፈፃሚ አካላት በሕገመንግስቱና በሕዝብ የተጣለባቸውን መብት ግዴታና አደራ አለመወጣታቸውንና ሕገመንግስቱን በመጣስ ከሕግ በላይ በመሆን በፍትህ አፈፃፀም ሂደት ውስጥ ጣልቃ እየገቡ ነው ወደሚል የኢፍትሃዊነት መገለጫ ወደሆነ መደምደሚያ አድርሶናል።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር፤

በመሆኑም፤ ክቡርነትዎና የፍትህ አስፈፃሚው አካላት ሕገመንግስቱንና የአገሪቱን የፍትህ ስርዓት በግንባር ቀደምትነት ከማክበርና ከማስከበር አኳያ ካለባችሁ ከፍተኛ ኃላፊነትና ግዴታ በመነሳት፤ ይህንን በማንኛውም መመዘኛ በፍትሃዊነት ሊፈረጅ ያልቻለውን የአቶ አሰፋ አብርሃን እስራትና መጉላላት ከሕገመንግስቱና ከሕግ አኳያ ተመልክታችሁ መብታቸው ተከብሮ በነፃ እንዲለቀቁ በአፅንዖት እንጠይቃለን።

ደግመን ደጋግመን በዜግነታችን የምናስምርበትና የምናስተጋባው አብይ ነጥብ፤ የኢፌዲሪ መንግሥት ተቀዳሚ ተግባርና ግዴታው ስለዜጎች መብትና ስለአገራችን ጥቅሞችና ሉዓላዊነት መከበር ዘብ የቆመውን የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን የአገራችንን ሕገመንግሥት በማክበርና በማስከበር፣ ፍትህ ሰፍኖ የሕግ የበላይነት ተረጋግጦ ሕዝቦች ከእርስ በርስ አተካራ ግጭትና ብሶት ተላቀው፣ መብት ነፃነታቸው ተከብሮ ትኩረታቸው ስለልማትና ስለዕድገት ብቻ የሚሆንበትን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ማረጋገጥ ላይ አፅንዖት እንዲሰጥ አጥብቀን በመጠየቅ ነው።

ከሰላምታ ጋር

በሰሜን አሜሪካ የትግራይ ተወላጆች
Email: justice4siye@Gmail.com

ለኢፌዲሪ መንግሥት የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
በፋክስ ሕዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል

ቅጂ፣

- ለተከበሩ አቶ ከማል በድሪ
  የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ኘሬዝዳንት
  በፋክስ ሕዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል
- ለተከበሩ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
  የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት ም/ኘሬዝዳንት
  በፋክስ ሕዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል
- ለተከበሩ አቶ ስዩም መስፍን
  የኢፌዲሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር
  በፋክስ ሕዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል
- ለተከበሩ አምባሳደር ተሾመ ቶጋ
  የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት አፈጉባኤ
  በፋክስ ሕዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል
- ለክብርት ወ/ሮ ሽታዬ ምናለ
  የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ም/አፈጉባኤ
  በፋክስ ሕዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል
- ለተከበሩ አቶ ደግፌ ቡላ
  የኢፌዲሪ የፌዴሬሽ ምክርቤት አፈጉባኤ
  በፋክስ ሕዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል
- ለተከበሩ አቶ መሐመድ ሰርሃዬ
  የኢፌዲሪ የፌዴሬሽ ምክርቤት ም/አፈጉባኤ
  በፋክስ ሕዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል
- ለተከበሩ ዶ/ር ካሣ ገብረህይወት
  በኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር
  በፋክስ ሕዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል
- ለተከበሩ አቶ አስመላሽ ወልደስላሴ
  በኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት
  የሕግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር
  በፋክስ ሕዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል
- ለተከበሩ አቶ ፋንታዬ ገዛኸኝ
  በኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት
  በፋክስ ሕዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል
  አዲስ አበባ
- ለተከበሩ ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሃቅ
  የተከበሩ የአገር ሽማግሌዎች ሕብረት
  በፋክስ ሕዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲደርሳቸው ተደርጓል
  አዲስ አበባ
- ለተከበሩ ዶ/ር ሳሙኤል አሰፋ
  በአሜሪካ የኢፌዲሪ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር
  በአካል በተወካዮቻችን እንዲደርሳቸው ተደርጓል
  ዋሽንግተን ዲሲ